ያ ትውልድ

ቀን ፡ መስከረም 1 ቀን 2014 ዓ.ም. (September 11, 2021)

## “ለ2014 ዓ.ም. እንኳን አደረሳችሁ”

*ከ«ያ ትውልድ ተቋም» የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ*

***ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፡***

እንኳን ለ2014 ዓ.ም. የዘመን መለወጫ በዓል አደረሳችሁ። ባህላችን ነውና እንኳን አደረሳችሁ፣ አደረሰን እንባባላለን። አዲስ ዘመን የሚባልበትም አሮጌው ዘመን ከነትዝታው፣ ከነችግሩ ለአዲስ ተስፋ፣ በጦርነት ላሉት ሰላም እንዲያመጣ፣ ለህመምተኞች ደህንነት እንዲሰጥልን፣ ለተከፉ የደስታ ዘመን እንዲያደርግላቸው ምኞታችንን “የሰላም፣ የጤናና የደስታ ዓመት ያድርግልን” ስንል እንገልፃለን። አሮጌው በአዲሱ መተካቱን ለማብሰር በየቤቱ፣ በየደጁ ችቦ ለኩሰን ወንዶች “በዮሃ አበባዬ” ሴቶች “በአበባየሆሽ” እናደምቀዋለን። ውብ በዓል! ድንቅ አዲስ ዓመት!

ሀገራችንን እና ሕዝባችንን መለስ ብለን ስንቃኝ ግን “ሁለት ሺህ አሥራ ሦስት ዓመት እንዴት ነበር?” ብንባል “ከሁለት ሺህ አሥራ አራት ይሻልል” ብንል የተሳሳትን አይመስለንም። ዓመት ከዓመት ሲለወጥ የሀገራችን ችግር በችግር እየጨመረ ለመምጣቱ ሁላችንም ምስክር ነንና። በእኛ ዕድሜ እንኳ መንግሥት ከመንግሥት ሲቀያየር ሰቆቃ በሰቆቃ፣ ግድያ በግድያ፣ ረሃብ በረሃብ፣ ድህነት በድህነት፣ ጦርነት በጦርነት ወዘተ. እየተደራረበ “ትሻልን ትቼ ትብባስን” እያየን ነው። ይህን ሂደት ለተገነዘበ እውን ዘመን መቀየሩ በዕድሜ ላይ አንድ ዓመት መጨመሩ ተመስገን ያሰኘን ይሆናል እንጂ ቀና ብለን ከተመለከትን ደሞ “ይህ ዓመት ምን ይዞ ይመጣ ይሆን” ከማለት ፈቀቅ አንልም።

በደምቢዶሎ የታገቱ ተማሪዎች ቤተሰብ፣ የሶማሌ ኢትዮጵያውያን አሰቃቂ ፍጅት፣ የሻሸመኔ፣ መተከል፣ ጋምቤላ፣ አጣዬ መሰል ጭፍጨፋና ካስከተለው መዘዝ ተርፈው የሚሰቃዩ ወገኖቻችንን ስንመለከት፣ ከወያኔ ጋር በተገባው ጦርነት አበሳቸውን ለሚያዩት የትግራይ አዛውንት እናትና አባቶች፣ ሕጻናት ስናስታውስ፣ እስካሁን መከራ ላልተለያቸው የአማራ ወገኖቻችን ፍጅትና መፈናቀል ስናስብ፣ በጥቅሉ ሙቀት፣ በርድና፣ ዝናብ የሚፈራረቅባቸው በየቦታው ተበትነው የሚገኙ ዜጎቻችንን ስናስብ፣ በአረቡ ዓለም እየተሰቃዩ አድኑን፣ ድረሱልን ባዮችን ስንቃኝ እውን አዲስ ዓመት አዲስነቱ ውስጣችን ደፍሮ ይዘልቃልን?

በርካታዎችን ባንጠቅስም ያለበደልና ግፍ በየእሥር ቤቱ የሚንገላቱ ወገኖችና ቤተሰቦች ሲታዩን፣ እነ እስክንድር ነጋን ጨምሮ  በቅርቡ የታሰሩት የ80 ዓመት አዛውንት አቶ ታዲዮስ ታንቱ ጉዳይ ስንቃኝ መንግሥት ባለበት ሀገር ፍትህ ሲጓደል እውን ለአዲሱ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ ብሎ ለመድፈር ይቻላልን?

“ያ ትውልድ ተቋም” ሰፋ አድርገን ስናየው ኢትዮጵያችን ለአለፉት 50 ዓመታት መከራዋና ችግሯ እየተንከባለለ ዛሬም ምድሯ የደም መሬት ሁኗል፤ አክልሜዳ። በጣት በሚቆጠሩ ብርቅዬዎች ግዞት መግባት፣ መታሰር፣ መሰወር፣ መገደል ብልጭታውን ያሳየው የሀገራችን ፖለቲካ ለደርግ የቤት ለቤት አሰሳ፣ ነጻ እርምጃ እና ቀይ ሽብር አሸጋግሮ ትውልድ ሲመትር “በቃ በለን” ያልነው ዘመን ለህወሓት አሸጋግሮ ሀገርና ትውልድ በቁም ጭምር ሲሞቱ እየዩ እያልን ኑረን፣ ሁሉን ችለን በ2011 ዓ.ም. እውን አዲስ ዘመን፣ አዲስ ተስፋ አሁን ገና መጣልን ብለን በእልልታና በጭፈራ ተቀብለን ወራት ሳንጓዝ ገጀራና ቆንጨራ ሰው አንገት ላይ ሲያርፍ፣ ቤቶች በእሳት ሲጋዩ ዜናው ሁሉ ታፈኑ፣ ታሰሩ፣ ተፈናቀሉ፣ ታረዱ፣ በጅምላ ተጨፈጨፉ ሌላም ሌላ የሰቆቃ ቃላት ለጆሮ እየደረሱ እነሆ! ዛሬም እንኳን አደረሳችሁ እንባባላለን።

“ያ ትውልድ ተቋም” ከተነሳበት ዓላማ አንዱ በያ ትውልድ የደረሰው ፍጅት ዳግም እንዳይደገም ትምህርት ይሆን ዘንድ በጊዜው የተፈጸሙ ስህተቶች ማስተማሪያ ሁነው ቀጣይ አገዛዝና ትውልድ ከእደዚህ ዓይነት ኢሰብአዊ አድራጎት በመቆጠብ ስለሀገርና ሕዝብ እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። በመሆኑም አሁንም በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን የዘር ጭፍጨፋ የምናወግዘው ስለ ሰባዊነት ስለምንሞግት ነው። ያለ አግባብ በየእሥር ቤቱ ያሉት እንዲፈቱ መጠየቅ ፖለቲከኝነት ሳይሆን ሰብአዊ ግዴታችን ነው። በጦርነቱ የተጎዱ፣ የተፈናቀሉትን ጨምሮ ስለ ሚሰዉት አቤት የምንለው የሰው ልጅ እልቂት ማብቃት አለበትና ነው። እናማ ይህንን ሁሉ ጉድ ተሸክመን ባህላችን ነውና እንኳን አደረሳችሁ፣ አደረሰን ብንባባልም ውስጣችን ግን እየዬ እያለ ነው፣ እጅግ በሀዘን ተውጠን ነው። አሁንም አዲሱ ዓመት ኢትዮጵያ ለልጆቿ በልጆቿ የምትሆንበት አዲስ ዘመን ይሆንልን ዘንድ መንግሥትን ሳይሆን ፈጣሪን ተንበርክከን እንለምናለን።

ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝባችንን ይጠብቅ!

ያ ትውልድ ተቋም

መስከረም 1 ቀን 2014 ዓ.ም. (September 11, 2021)